

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከሴፕቴምበር 1-30/2025 የነበረዉ የአየር ጠባይ ግምገማ

# እንዲሁም ከኦክቶበር 1-31/2025 የሚኖረዉ የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ

ባለፈዉ የሴፕቴምበር ወር በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ የሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ አና ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም ከወሩ አጋማሽ በዋለ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከነበረዉ የደመና ሽፋን መጨመር ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በ 24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 32፣ 30.1፣ 37.4፣ 32.4፣ አርባምንጭ 63.7፣ አዋሳ 33.4፣ ባህር ዳር 33.7፣ 55.4፣ 43.4፣ 41፣ ደብረ ማርቆስ 49.4፣ ጎንደር 71፣ 38.6፣ ጎሬ 44.3፣ 35.7፣ መቀሌ 33፣ 36.5፣ ነቀምቴ 37.4፣ 43.4፣ 67፣ አዲሰ አበባ ጥቁር አንበሳ 37.5፣ 59.8፣ አቦምሳ 35.2፣ አደዋ 34፣ አይራ 30.5፣ 47.3፣ 47.8፣ 44.5፣ 32፣ 35.5፣ አልጌ 43፣ ሐሮማያ 44.5፣ አምደወርቅ 73.4፣ አማን 30.8፣ አንገር ጉትን 64.6፣ 60፣ 34፣ 34፣ 46.2፣ 32.4፣ አርጆ 46.4፣ 36.6፣ አርሲ ሮቤ 81.3፣ 33.8፣ በደሌ 41.5፣ 43.4፣ 44.4፣ አዋሽ አርባ 30፣ ቡለን 30.4፣ 30.5፣ 46፣ 40.2፣ 34.2፣ 30.5፣ አሶሳ 36፣ ጭራ 42.4፣ ዳንግላ 31.5፣ ቻግኒ 50.4፣ 30፣ 31.6፣ 37.6፣ ጨዋቃ 40፣ 30፣ 48፣ ዳሊፋጊ 38፣ ደበረ ታቦር 37፣ 34.5፣ 30፣ ኢጃጂ 42.7፣ ፍቼ 35.8፣ ፉኙንዶ 75፣ 82.5፣ 56፣ ገለምሶ 37.2፣ ጋምቤላ 30.7፣ ጋቲራ 31.7፣ ጊዳ ኢያና 66.5፣ 32.6፣ 33፣ 52.9፣32.9፣ ጂንካ 41.7፣ ጊምቢ 42.5፣ 31.3፣ 55.1፣ ጃራ 38.2፣ ካቺሴ 38.9፣ 38፣ 56፣ ኮንሶ 33፣ 38.7፣ ላሬ 51፣ ምዕራብ አባያ 39፣ ፓዌ 39.4፣ ወራቤ 33.7፣ ባቱ 33፣ ማንኩሽ 53.6፣ 45፣ መተማ 34.6፣ 30፣ 38.2፣ ሞጣ 40.2፣ ሰንቃጣ 31፣ ሻሁራ 42፣ ሽሬ 52.9፣ 33.7፣ ሽርቆሌ 36.3፣ አቦ ሞሪንጋ 41፣ 39.8፣ 45.2፣ አዲስ ዘመን 42፣ አዲ አርቃይ 30.1፣ 30፣ አለታ ወንዶ 30.8፣ አታንጎ 34.5፣ 45.5፣ 31.2፣ 49፣ 54.5፣ አሮርሳ 32.2፣ ቢላምቢሎ 33.1፣ 39.6፣ 37፣ ቦርቃ 41.8፣ 44.8፣ ቡልቂ 36.7፣ 30.2፣ ጨፌ ዶንሳ 37.3፣ ደራ 35.5፣ መንደር ሰባት 146.4፣ 30.7፣ ዳራ ማሎ 30፣ 30፣ 30.2፣ ሃራ 30፣ 30.4፣ ደበረ ሲና 43.9፣ 35.7፣ 34.3፣ ድልቢ 32.2፣ እርምጭ 35.7፣ ጋሽና 32.7፣ ጊናገር 43.9፣ 35.6፣ጎሮ 36፣ ሃርቡ 30.2፣ 60.3፣ 30.2፣ ሆሮዶይ 46.4፣ ሃሮ 30.4፣ 40.2፣ 50.1፣ 40.4፣ ቅዳሜ ገበያ 48.6፣ 39.8፣ 56.4፣ 57.4፣ 48.7፣ 58.6፣ 52.8፣ 34.8፣ 56.6፣ ኩሚ 33.8፣ ኮበን 35፣ 43፣ ኩረፋ ጨሌ 31.5፣ ቁሉቢ 57.7፣ ላንጌ 30፣ መሆኒ 30.9፣ ሙጊ 33.1፣ ማርዬ 50.9፣ መቂ 63.2፣ ኦሞ ናዳ 40.2፣ ኦንጋ 37.5፣ 43.3፣ 42፣ 33.7፣ 34.8፣ ሰቆጣ 35.6፣ ሸንዲ 34.5፣

31.5፣ ተርኮዲ 103.2፣ 33.8፣ ፅገሬዳ 33.7፣ ዪና 36.5፣ ይርጋለም 36.5፣ ያንፋ 34.2፣ 41.3፣ 33.2፣ 45.3፣ 32.8፣ 40.3፣ ያዮ 31.8፣ 41.6፣ ዪጪላ 40.3፣ መንድር 11 185፣ 35፣ ሲቦ 42፣ እዳግ አርቢ 42.2፣ አዳሚ ቱሉ 32፣ 38.2 እንዲሁም ከርሳ 35.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፈዉ የሴፕቴምበር ወር በ111 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 60.3 - 185 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ70 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል መንድር አስራ አንድ፣መንደር ሰባት፣ ተርኮዲ፣ ፓዌ፣ ፉኙዶ፣ አርሲ ሮቤ፣ አምደ ወርቅ፣ ማንኩሽ፣ ጎነደር፣ ይገኙበታል (ምስል 1)፡
፡





ምስል፡1 ከሴፕቴምበር 1-30 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉዉ የሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ151-830 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ11-28 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሓረርጌ ዞኖች፤ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጊዲዮና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣ ላይ ከ51-150 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-14 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት


ባለፉዉ ሴፕቴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሓረርጌ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ጉጂ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎና የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ ጋም፣ ወላይታ፣ ጌዲዮና ባስኬቶ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ ጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ እና የሊበን ዞኖች፣ ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከመሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ፍሬ በመሙላትና በማበብ ላይ ባሉ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር ጠቀሜታዉ የጎላ ነበር፡፡ እንዲሁም ቀስ በቀስ በተለይም በሁለተኛው እና የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ላይ ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች የተስፋፋዉ እርጥበት በአካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ ከመኖሩም በላይ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው (ካርታ 4 )።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር በአባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ በላይኛውና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ አዋሳኝ ቦታዎች እንዲሁም በጥቂት የአፋር ደናከል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የተከዜ፣ የአዋሽ፣ የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች መጠነኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ወር የነበረው የገጸ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ፍሰት የተሻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወደ ግድቦችና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የገባው የዉሃ መጠን ጨምሯል፡፡ ስለሆነም ለሀይል ማመንጫነትም ሆነ ለመስኖነት ለሚያገለግሉ ግድቦች የተሻለ የውሃ ግብዓት እንደነበረ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፣ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በኦክቶበር እና በመጀመሪያዎቹ በኖቬምበር አስር ቀናት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ነው። በመደበኛ ሁኔታ በሀገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ የበጋ ወቅት ዝናብ ከኦክቶበር መጀመሪያዎቹ ቀናቶች ጀምሮ መዝነብ ይጀምራል፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ድንበር ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው የበጋ ወቅት እንደሚስተዋለው የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ከመታየቱ አንጻር የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመር ያሳያል፡፡

በመጪዉ የኦክቶበር ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና በሂደትም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሁኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ሀይል በመታገዝ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በጥቂት የምዕራብና በደቡብ ምዕራብ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31፣ 2025 የሚኖረው የዝናብ መጠን

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦክቶበር ወር በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው ቀጣይነት ያለው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች አንታዊ ጎን ይኖረዋል። በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሣር ልምላሜ መሻሻል የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ሆኖም ግን በወሩ የሚኖረው እርጥበት እንደ ዋግ የመሳሰሉ የሰብል በሽታዎች እንዲከሰቱ ምቹ ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት የማሳ ጉብኝት በማድረግ ምልክቶች ሲታዩ አፋጣኝ እርመጃ ለመውሰድ የሚያስችል ዝግጅት ማደረግ ያስፈልጋል። በሂደትም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄደው እርጥበት ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና ሰብል አምራች በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በስፋት በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ

እንደሚኖረው ይጠበቃል። በአንጻሩ ግን አልፎ አልፎ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ የሚጠበቀው ከፍተኛ እርጥበት በተለይም በደረሱ ሰብሎች ላይ አሉታው ተፅእኖ የሚኖረው በመሆኑ የደረሱ ሰብሎችን ባሉት ደረቅ ሰሞናት መሰብሰብ ይገባል። ሆኖም ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች በወሩ የሚገኘውን የዝናብ ውሃ በመሰብሰብና በአግባቡ በማከማቸት በቀጣይ በጋ ደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የኦክቶበር ወር የሚጠበቀው የዝናብ ሁኔታ በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የባሮ አኮቦ፣ የታችኛው አባይ እና የኦሞ ጊቤ እንዲሁም የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጨመር የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች የተሻለ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው የሚያስችል ሲሆን በተጨማሪም በመጠኑም ቢሆን ለከርሰ ምድር የውሀ ይዘትን መሻሻል አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በተለያዩ ውሃ አጠር ተፋሰሶች የሚጠበቀው እርጥበት የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን እንደጨምር ይጠበቃል። በሌላ በኩል የበጋ ተጠቃሚ የሆኑት አብዛኛው የገናሌ ዳዋ፣ የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌና የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ሲሆን በአንጻሩ ግን የአፋር ደናክል፣ የአዋሽ፣ የተከዜ፣ የላኛው አባይ፣ ጥቂት የላይኛው ኦሞ ጊቤና የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ።